የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

June 8, 2026
Addis Ababa, Ethiopia

# ECMA Licenses United Capital Financial Services PLC as Investment Bank

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) has granted a Capital Market Service Provider (CMSP) license to United Capital Financial Services PLC, a subsidiary of United Capital Group Nigeria, making it the first foreign investment bank to establish a subsidiary in Ethiopia.

The license authorizes the company to operate under the Investment Banking category. The Authority has also approved the appointment of five Board Directors and licensed four Appointed Representatives within the company.

Issued on Friday, June 5, 2026, the license brings the total number of licensed CMSPs in Ethiopia to 18 and the number of investment banks to 7, reflecting the tangible and continuous development in the operationalization and expansion of the country's capital market.

At the official licensing ceremony, the Director General Hana Tehelku noted that the entry of a Pan-African institution such as United Capital marks a historic milestone in the development of Ethiopia's capital market, further indicating that the event demonstrates strong confidence in the credibility of the country's emerging financial ecosystem and the direction of ongoing reforms.

She noted that such developments reflect growing recognition of Ethiopia's market potential and institutional progress, and can contribute to strengthening the depth, capacity, and regional integration of the market, while underscoring the importance for licensed service providers to adhere to the highest standards of market conduct, governance, and regulatory compliance.

ECMA remains committed to fostering a fair, transparent, and efficient capital market ecosystem that supports sustainable economic growth and enhances investor confidence.

The Ethiopian Capital Market Authority congratulates United Capital Financial Services PLC and its parent company, United Capital Group, on this milestone and looks forward to their contribution to the ongoing development of Ethiopia's capital market.

**For enquiries & additional information contact**

Contact: Communications & Public Relations Directorate

Phone: 011 557 81 19

Email: communication@ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

ሰኔ 01 ቀን 2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለዩናይትድ ካፒታል ፋይናንሻል ሰርቪስስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር የኢንቨስትመንት ባንክ ፈቃድ ሰጠ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን (ባለስልጣኑ) የናይጄሪያው ዩናይትድ ካፒታል ግሩፕ ተቀጥላ ኩባንያ (Subsidiary) ለሆነው ዩናይትድ ካፒታል ፋይናንሻል ሰርቪስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ሰጥቷል።

ይህም ተቋሙን በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥላ ኩባንያ በማቋቋም እንዲንቀሳቀስ ፈቃድ የተሰጠው የመጀመሪያው የውጭ ኢንቨስትመንት ባንክ ያደርገዋል። የተሰጠው ፈቃድ ድርጅቱ በኢንቨስትመንት ባንክ ዘርፍ ስር እንዲሠራ የሚፈቅድ ሲሆን፤ ባለስልጣኑ ከዚህ በተጨማሪ የአምስት (5) የቦርድ ዳይሬክተሮችን ሹመት ያጸደቀ ከመሆኑም በላይ ለአራት (4) ተሿሚ እንደራሴዎችም ፈቃድ ሰጥቷል።

አርብ ግንቦት 28 ቀን 2018 ዓ.ም በይፋ የተሰጠው ይህ ፈቃድ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የተፈቀደላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን ጠቅላላ ቁጥር ወደ አስራ ስምንት (18)፣ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ባንኮችን ቁጥር ወደ ሰባት (7) ከፍ አድርጎታል። ይህም የሀገሪቱ የካፒታል ገበያ ተግባራዊነት እና ልማት እያሳየ ያለውን ተጨባጭና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ያሳያል።

በይፋዊው የፈቃድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ላይ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሃና ተኸልቁ እንደገለጹት፣ እንደ ዩናይትድ ካፒታል ያለ የፓን-አፍሪካዊ ተቋም ወደ ገበያው መግባቱ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ዕድገት ላይ ታሪካዊ ምዕራፍ እንደሆነ ገልጸው፤ ሁነቱ እያደገ ባለው የሀገሪቱ የፋይናንስ ሥነ-ምህዳር ተዓማኒነት እና እየተከናወኑ ባሉ የማሻሻያ እርምጃዎች ላይ ጠንካራ እምነት መኖሩን እንደሚያሳይ አመልክተዋል።

ዋና ዳይሬክተሯ አክለውም፣ እንዲህ ያሉ ዕድገቶች ለኢትዮጵያ የገበያ አቅም እና ለታየው ተቋማዊ መሻሻል የተሰጡ ትልቅ እውቅናዎች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የገበያውን ጥልቀት፣ አቅም እና ቀጣናዊ ውህደት ለማጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ አመልክተዋል።

በተመሳሳይም ፈቃድ የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪዎች ከፍተኛ የገበያ ሥነ-ምግባርን፣ የኮርፖሬት አስተዳደር መርሆዎችን እና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማክበር እንዳለባቸው አፅንዖት ሰጥተው አሳስበዋል::

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን የሚደግፍ እንዲሁም የኢንቨስተሮችን እምነት የሚያጎለብት ፍትሃዊ፣ ግልጽ እና ቀልጣፋ የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ለመገንባት ያለውን ጽኑ ቁርጠኝነት በድጋሚ ያረጋግጣል።

ባለስልጣኑ ለዩናይትድ ካፒታል ፋይናንሻል ሰርቪስስ ኃ.የተ.የግ.ማ. እና ለእናት ኩባንያው ዩናይትድ ካፒታል ግሩፕ ለዚህ ስኬት የተሰማውን ደስታ እየገለጸ፣ ተቋማቱ ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ቀጣይ ልማት ለሚያበረክቱት አስተዋጽኦ መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

---

### ለጥያቄዎችና ተጨማሪ መረጃ

**የኮሙኒኬሽን እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት**
**ስልክ: 011 557 81 19**
**ኢሜይል: communication@ecma.gov.et**